Terrorism

Dr. Taye W/. Semayat et.al    Fsc.

13

የወ/ይ/መ/ቁ.4348

ግንቦት 02 ቀን 1994 ዓ.ም.

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሀሳዕና ነጋሽ

አሰግድ ጋሻው

ይግባኝ ባዮች፡- 1. ዶክተር ታየ ወልደሰማያት ቀረቡ:: ጠበቃ አበበ ወርቁ ቀረቡ

2. አቶ ገ/ጻድቅ ገ/ማርያም ቀረበ::

3. መቶ አለቃ ጫኔ ታለ ቀረበ::

4. አቶ ታለጌታ ልዑል/ዳኜ/ ኃ/ማርያም አልቀረበም::

5. ሻምበል ሞገስ አሰፋ ቀረበ::

ዐቃቤ ሕግ፡- አቶ እዮብ ገ/ሕይወት

ይግባኝ ባዮች ይግባኛቸውን ያቀረቡት በተለያየ መዝገብ ሆኖ ክርክሩም የተጠናቀቀው በዚሁ መልክ ቢሆንም በሥር ፍ/ቤት የተከሰሱትና ውሣኔም የተሰጠው በአንድ መዝገብ ስለሆነ ይግባኛቸውንም በአንድነት መርምሮ መሥራት ተገቢ ሆኖ ስላገኘነው አምስቱንም መዝገቦች በዚህ መዝገብ አጠቃለን የሚከተለውን ወስነናል::

## ው ሣ ኔ ፣

ዓቃቤ ሕግ በሥር ፍ/ቤት በይግባኝ ባዮች ላይ የመሠረተው ክስ ለወንጀል ሥራ ግብረአበር በመሆን የኢትዮጵያን መንግሥት በኃይል ለመጣልና ሕዝብን የጦር መሣሪያ በማስያዝ ለሁከትና ሽብር ፈጠራ አድራጎት ለማስነሳት በማቀድ 1ኛ እና 2ኛ ይግባኝ ባዮች በሥር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ ከነበረው ግለሰብና ካልተያዘው ስለሽ ብርሃኔ ጋር ከታህሣሥ ወር 1987 ዓ.ም. ጀምሮ በተለያዩ የፖለቲካ አጀንዳዎች ላይ ውይይት በማድረግ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት እነሱ ከሚፈልጉት ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አመራርና አመለካከት አላራመደም በሚል የጋራ አቋም በመያዝ የሁከትና ሽብር ፈጠራ ሥራን የሚያራምድ የታጠቀ አንድ ተቀዋሚ ድርጅት ለማቋቋም ተስማምተው 1ኛ ይግባኝ ባይ የዚሁ ድርጅት ሊቀመንበር በሥር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ የነበረው ፀሐፊ፣ የአሁኑ 2ኛ ይግባኝ ባይ በኮሚቴ አማራር ባይኖርም የድርጅታቸው ሥራ በአገናኝነት ፈፃሚ ያልተያዘው ስለሽ ብርሃኔ ገንዘብ ያዥ በመሆን ከላይ በተጠቀሰው ዓ.ም. አጋማሽ በግዮን ሆቴል ባደረጉት ስብሰባ ከተመራረጡ በኋላ ይህ እነሱ ያቋቋሙቱ የፖለቲካ ድርጅት በአገሪቱ በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች መሠረት በሕግ ዕውቅና ሳያገኝ መጠሪያ ስሙ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ............ ቀን ............

እንዲሆንና የግንባሩ የፖለቲካ ፕሮግራም ከግቡ እንዲደርስ ለማስፈፀሚያ XYZ ጽ/ቤት በሚል የአጭርና የረጂም ጊዜ ዕቅድ በመንደፍ፣

1. በአጭር ጊዜ ዕቅድ የገቢ ማስገኛ ምንጭ በሚል ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን በመለየት በስምምነት ካልተቻለም በማግባባት ለድርጅቱ መዋጮ እንዲያደርጉ፤

2. ፈቃደኛ ያልሆኑትን የግዴታ ክፍያ መጠን መወሰን በኃይልና በማስፈራራት መዋጮ እንዲያደርጉ ማድረግ፤

3. መዋጮ እንዲያደርጉ የሚፈለጉትን ሰዎች በመከፋፈል፣

4. ከላይ የተጠቀሰውን ዓላማ ለማስፈፀም ወታደራዊ ብቃት ያላቸውን ሰዎች በመመልመል ትጥቅ አስይዞ ከግለሰቦች ሀብትና ገንዘብ በኃይል መውሰድ ወታደራዊ ቡድን በትጥቅ የተደራጀና በስኳድ ደረጃ እንዲሆን፣

5. መንግሥታዊና የንግድ ድርጅቶችን መዝረፍ በኢኮኖሚ ተቋሞች፣ በመገናኛ መስመሮች ላይ እንቅስቃሴ በሚያደርጉ ተሽከርካሪዎች ላይ አደጋ በመጣል ዘረፋ ማካሄድ፤

6. በአገሪቱ ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አለመኖሩን ለማሣየት በውጭ አገር ዜጎች ተቋሞች ላይ አደጋ መጣል፤

7. በመንግሥስት ባለሥልጣኖች ወይም የመንግሥት ደጋፊ ናቸው በሚሏቸው ላይ አደጋ መጣል፤

የሚሉና ሌሎች እቅዶችን በመንደፍ እነዚህን ለመፈፀም እንዲችሉ፣

1. ወታደራዊ ብቃት ያላቸውን ሰዎች በመመልመል፣

2. የጦር ማሣሪያ በግዥ በማሰባሰብ ላይ ተስማምተው የተለያዩ የጦር መሣሪያዎችን ካዘጋጁ በኋላ 3ኛ፣4ኛ እና 5ኛ ይግባኝ ባዮችንና ሌሎችን መልምለው በቅድሚያ በ1ኛ ይግባኝ ባይ በፅሑፍ ዝርዝር የተዘጋጁት ሰዎች የሚከፍሉት የገንዘብ መጠንን በመወሰን የጥሪ ደብዳቤ በማዘጋጀት ከዚህም አልፈው በመንግሥት ኃላፊነት ላይ ወይም የመንግሥት ደጋፊዎች በሚሏቸው፣

1. አቶ ዳዊት ዮሐንስ የተወካዮች ም/ቤት አፈጉባኤ፣
2. ዶክተር ዱሪ መሀመድ (ሚኒስትርና አምባሳደር የነበሩ፣)
3. ዶክተር አብዱልመጂድ ሁሴን (ሚኒስተር የነበሩ)
4. አቶ ክፍሌ ወዳጆ የቀድሞ ተወካዮች ም/ቤት አባል፣ ሕገ መንግሥት
   ጉባኤ ሊ/መ
5. አቶ ሀሰን አብደላ ሚኒስተር

6. ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ ላይ የግድያ እርምጃ እንዲወሰድ ወስነው ፕሮፌሰር እንድሪያስን ለመግደል የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዲበረታ ክትትል ሲያደርጉ በመቆየታቸው በቀጣዩ ደረጃም የውጭ አገር ዜጎችና ተቋሞች ላይ እርምጃ ለመውሰድ በተስማሙት መሠረት፡-

ፌዴራል ጠቅላይ [illegible] ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን

15

1. በየካቲት ወር 1987 ዓ.ም. በሁሉም ተከሳሾች ስምምነት በአሁን 2ኛ ይግባኝ ባይ አስፈፃሚነት አደጋ አድራሽ ቡድን አደራጅተው በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ በሚገኝ በአሜሪካን ዕርዳታ ድርጅት ጽ/ቤት ላይ ቦንብ እንዲጣልና ፍንዳታ እንዲደርስ በማድረጋቸው፣

2. በዚሁ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 28 ክልል ውስጥ በመንገዝ ላይ የነበሩትን ሚስተር ሮጊ ሮበርትና ገቢ ጆባኒ የተባሉትን በመኪናቸው ውስጥ እንዳሉ በመስከረም ወር 1988 ዓ.ም. የዚሁ ድርጅት ታጣቂ ቡድን አፍኗቸው ለተወሰነ ሰዓት በአካባቢው በአንድ ቤት ውስጥ ካስቀመጣቸው በኋላ መኪናቸውን ነጥቆ በመውሰዱ፣

ተከሣሾች (ይግባኝ ባዮች) በሕግ የተቋቋመውን መንግሥት በኃይል ለመጣስ በህግ እውቅና ያላገኘና የታጠቀ የፖለቲካ ድርጅት አቋቁመው የጦር መሣሪያ በያዘ የሽብር ፈጠራ ቡድን ውስጥ መሪና አባል በመሆን በአገሪቱ ውስጥ ለሽብር ፈጠራና ሁከት አድራጎት በመነሳታቸው ተከሰዋል የሚል ሲሆን የተጠቀሰባቸውም የወ/መ/ሕግ ቁጥር 32(1)(ሀ) እና 252(1)(ሀ) ነው።

ዓቃቤ ሕግ በክሱ የተመለከቱ ድርጊቶችን ያስረዱልኛል ያላቸውን የሰውና የፅሑፍ ማስረጃዎችን አቅርቦ ይግባኝ ባዮችም እንዲከላከሉ በተበየነው መሠረት የመከላከያ ማስረጃዎቻችን ናቸው ያሏቸውን አሠምተዋል። ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ማስረጃዎች መርምሮ ይግባኝ ባዮችን ከላይ በተጠቀሰው ሕግ ሥር ጥፋተኛ በማድረግ እንደቅደም ተከተላቸው በ15፣ በ13፣ በ10፣ በ8 እና በ8 ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጡ ወስኖባቸዋል።

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ባዮች ያቀረቡትን የይግባኝ ማመልከቻ ፍሬ ሃሳቦች እንደሚከተለው አስፍረናቸዋል።

የ1ኛ ይግባኝ ባይ ጠበቃ ታህሣሥ 14 ቀን 1992 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ የቀረበው የይግባኝ ቅሬታ በዶክተር ታየ ላይ የቀረቡት ሁለት ምስክሮች የራሳቸውን ድርጊት በማስቀደም ምስክርነታቸው እንዲታመን ለማድረግ የጣሩና በተለይም ዶክተር ቀኛዝማች ሰለሞን ሌሎችን ተከሣሾች ጭምር በዶክተር ታየ ላይ መስክረው ነፃ ቢወጡ የሚሻላቸው መሆኑን ሲመክሩ የነበሩ ናቸው፤ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት ሁሉ በሁለቱ ምስክሮች አማካኝነት የተቀነባበረ ነው ከሚያሰኝ ግምት ላይ ያደርሣል፤ ተከሣሽ የነበሩትና በመሞታቸው ክሱ የተቋረጠላቸው አቶ ከበደ ደስታ ዓቃቤ ህግ በዶክተር ታየ ላይ ከመሠከሩ የማይከሰሱ መሆናቸውን የገለፁላቸው መሆኑን ለፍርድ ቤቱ መግለፃቸው ይህን ግምት እውነታ ያደርገዋል፤ የእነዚህ ሁለት ምስክሮች የምስክርነት ቃል የተደጋገፈ ተደርጎ በፍርድ ቤቱ መቀጠሩ ትክክል አይደለም፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር የተባለው ተቋቋመ የሚሉት ግንባር እነሱ የፈጠሩትና በኋላ ሌሎች ሰዎች አብረዋቸው እንደነበሩ ለማስመሠል የሞከሩበት እንጂ ይግባኝ ባዩ የሌሉበት ግንባር ነው፤ ቃለ መሀላ ተፈፀመ፤

ፌዴራል ጠቅላይ ... ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ..... ቀን .....

ተመራርጠን ዶክተር ታየ ሊቀመንበር ሆነው ተመረጡ ያሉት ሁሉ የሁለቱ ሰዎች ፈጠራ እንጂ እውነትነት ያለው አይደለም፤ የሁለቱ ምስክርነት በሚታመን ገለልተኛ ምስክር የተደገፈ አይደለም፤ የሲፍ/ቢረሳው/ የተባለው ምስክር ወንጀሉን ሁሉ ራሱ የፈፀመ ራሱ ፍርድ ቤት ቀርቦ ያረጋገጠ መሆኑ እየታወቀ በሌሎች ንፁህን ሰዎች ላይ የሰጠው ሀሰተኛ ምስክርነት እንዴት ሊታመን ቻለ? ዶክተር ቀኛዝማች ሰለሞንም መሣሪያ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላ ሲያንቀራጥጡ የነበሩ መሆናቸው በራሳቸው የተረጋገጠ ናቸው፤ ወንጀል ፈፃሚዎቹ እነርሱ መሆናቸው በራሳቸው እየተረጋገጠ ሌላ ሰው እንዲወነጅሉ መደረጉ ከፍተኛ ስህተት ነው፤ ስለዚህ ምስክርነታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል።

ከዶክተር ታየ ቤትና ቢሮ ተገኙ የተባሉ ሰነዶች እሳቸው በሌሉበት ተገኙ የተባሉ የፈጠራ ሰነዶች ናቸው፤ ይህን የመሠከሩት የራሱ የምርመራ ክፍሉ የፖሊስ ባልደረቦች ናቸው፤ ፍትሻው ይግባኝ ባዩ በሌሉበት መደረጉ ከፍተኛ ጥርጣሬ ሊጣልበት ይገባል፤ XYZ የሚለውም ሰነድ የሚያቋቁመው የወንጀል ድርጊት የለም።

የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል የሚያፈርሰው የይግባኝ ባይ 1ኛ መከላከያ ምስክር ውድቅ የተደረገው እና ፍርድ ቤቱ ምስክሩ ቀደም ሲል በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.27 እና 35 መሠረት የሰጡትን ቃል በማገዘብ ውድቅ ማድረጉ በሕግ የተደገፈ አይደለም። ሁለተኛ የመከላከያ ምስክርም ተገኘ የተባሉትን ሰነዶች በሚመለከት ብርበራው የማይታመን መሆኑን በሚያረጋግጥ ሁኔታ የፈረመችው ሳይነበብላት እንዳሆነ የመሠከረችውን ፍ/ቤቱ ላንብብ ብላ አልጠየቀችም ማለቱ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ቃል የተቀነባበረ እንጂ እውነተኛ አለመሆኑን ለማስረዳት የቀረበውን የደክተር ታየን ነጥብ ማዳከሚያ አይሆንም ፍ/ቤት ምስክርነቱን የጣለው ያላግባብ ነው፤ የፅሑፍ ማስረጃዎቹ ከይግባኝ ባይ ቤትም ሆነ ቢሮ አልተገኙም፤ እነዚህ ሰነዶች ዶክተር ታየ ከተከሰሱበት ጉዳይ ጋር ምንም ግንኙነት የላቸውም ሰነዶች ከይግባኝ ባዩ ቤት ተገኙ የተባለው እውነት አይደለም እንጂ እውነት ቢሆን እንኳን እንደክሱ ዓይነት የሚያስረዳ አይደሉም፤ የቴክኒክ ምርመራ መግለጫን በተመለከተ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ ተከሳሹ(ይግባኝ ባይ) እንዲከላከሉ ብይን ያልሰጠ ሲሆን በፍርዱ ላይ ግን "በሦስተኛ ገፅ ጀርባ ተዘቅዝቆ በእንግሊዘኛ ዊዝ ዋርኒግ 10,000 የሚል እና በአማርኛ የእጅ ፅሑፍ የተለየዩ ሰዎች ስም ዝርዝር የያዘው ደግሞ የ1ኛ ተከሣሽ መሆኑ ተረጋግጧል" የሚል አስፍሯል። ይህ የምርመራ ውጤት ለዶክተር ታየ ካለመድረሱም በላይ በዚህ ነጥብ ይከላከሉ አልተባለም። ፅሕፈቱም የዶክተር ታየ አይደለም፣ ዶክተር ሰለሞን የተባሉት ምስክር ራሳቸው ፅሑፈቱ የራሳቸው ሊሆን እንደሚችል ገልፀዋል። ስለዚህ ይግባኝ ባይ እንዲከላከሉ ባልተወሰነበት ነጥብ ፁሑፉ የይግባኝ ባይ መሆኑ ተረጋግጧል ተብሎ የጥፋተኛነት ውሣኔ በዚህ ላይ መመሥረቱ ትክክል አይደለም፤ ስለሆነም የሰው ምስክሮችና የፁሑፍ ማስረጃዎች ድርጊቱን ያላስረዱ ከመሆኑም በላይ የዶክተር ታየ ምስክሮች የዓቃቤ ሕግን ምስክሮች ቃልና የፅሑፍ ማስረጃ ያፈረሱ በመሆኑ፣ ተፈፀመ የተባለው ድርጊት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ......... ቀን .........

14

"የጦር መሣሪያ ይዞ እንዲነሳ የማድረግ ሁከት በማንሳት ወይም የጦር መሣሪያ የያዙ ሽፍቶች በማስነሳት ሽብር ያነሳ ወይም ለማንሳት የፈለገ እንደሆነ" የሚለውን ኃይል ቃል የሚያሟላ ስላልሆነ የጥፋተኛነት ውሣኔ ይሻርልኝ፤

የቅጣት ውሣኔን በሚመለከት ፍ/ቤቱ ቅጣት ሊከብድ ይገባል ካለባቸው ነጥቦች ውስጥ ዋነኛው ምክንያት ዶክተር ታየ ተቋቋመ የተባለው ግንባር "መሪ" ናቸው በማለት ነው፤ ይህ እንደማክበኛ ሊወሰድ የገባ የነበረው ዶክተር ታየ "ግንባር" የተባለውን ድርጅት ሃሳቡን እንጂ ፀነስ አድርገው፣ ቅስቀሳው አሰባሰበው ዋናው መሪ እሳቸው ሲሆኑ ነበር፤ ተመስክሯል በተባለው ደረጃ እንኳን ቢወሰድ ዶክተር ታየ ሊቀመንበር ሆነው በስብሰባው ላይ ተመረጡ ከመባል በስተቀር በመሪነት አደረጉ የተባለ ነገር የለም፤ ቅጣቱን በሕጉ ከተቀመጠው መነሻ በማራቅ እንዲከብድ መደረጉ ያላግባብ ስለሆነ ቅጣቱን በመቀነስ ይህንኑ ቅጣትም በመገደብ ይግባኝ ባይ እንዲሠናበቱ የሚጠይቅ ነው።

የ2ኛው ይግባኝ ባይ ጠበቃ ኅዳር 27 ቀን 1992 ዓ.ም. በተፃፈ የይግባኝ ቅሬታ ማመልከቻ ያቀረበ ሲሆን ፍሬ ነገሮቹን እንደሚከተለው መዝግበናል።/

ዮሴፍ ወይም ቢረሳው የሚባለው የዓቃቤ ሕግ ሁለተኛ ምስክር በ1985 ዓ.ም. ኅደር ወር መጨረሻ አካባቢ 1ኛ/ ተሾመ ቢምረው 2ኛ/ አብይ 3ኛ/ ሽመልስ ከሚባሉ ሦስት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጋር ሆኖ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር(ኢብአግ) የሚባል የፖለቲካ ድርጅት መመስረቱን፣ ተሾመ ቢምረውን ፖሊስ ሲይዘው እሱ መሸሸጉን ከዚያም በ1987 ዓ.ም. በUSAID ግቢ ቦምብ ማፈንዳቱን፣ እንዲሁም ሲ.ኤም.ሲ. መንገድ ላይ ሁለት ፈረንጆች ይጓዙበት የነበረ መኪና መንጠቁን፣ ለዶክተር ሰለሞን አበበ የጦር መሣሪያ እንዲያስቀምጥለት መስጠቱን ለፖሊስ ገልጿል፣ እሱ ሳይከሰስ እኔ ምንም የማላውቀው ንፁሕ ሰው ተከስሼ እሱ እንዲመሠክርብኝ ተደርጎ ተፈርዶብኛል፤ ለጦር መሣሪያ መግዣ ብር 6000 ከሳሹ ብርሃነ ወሰኜ ለቢረሳው ሰጠሁ፣ መሣሪያውን ተቀብየ አስቀመጥኩ ያለው 1ኛ የዓቀቤ ሕግ ምስክር ዶክተር ሰለሞን አበበ ከክስ ነፃ ተደርጎ በእነሱ የሀሰት ምስክርነት ብቻ ተፈርዶብኛል፤ ምስክሮቹ ከመሠከሩ በነፃ እንደሚለቀቁ ፖሊስ ስለነገራቸው መስክረው የዳኑ ናቸው፤ ራሱን የወንጀል ተዋናይ አድርጎ የቀረበ ሰው ምንም በማያውቅ ሌላ ሰው ላይ መስክርበትና አትከሰስም ከተባለ፣ ፍ/ቤትም ይህን የሚቀበል ከሆነ ተከሳሽ ከመቀጣት ማን ሊድን ይቻላል? በእኔ ላይ ይህ በደል የተፈፀመብኝ በሕግ ተፈቅዶለት በሚንቀሳቀሰው መአህድ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ስላደረግሁ ብቻ ነው፤

1ኛና 2ኛ የዐቃቢ ሕግ ምስክሮች ያልመሰከሩብኝ የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ ለማንሳቱ ድጋፍ የሚሆን ነገር የግንባሩን አባላት ያማክር ነበር፣ በ1985 በጥሩት ተቋቁሞ በ1988 በተጠናከረው ግንባር መካከል ለተፈጠረው ግንኙነት መሠረት የሆነው እሱ ነው፣ 2ኛ የዐቃቢ ሕግ ምስክርን ለተከሳሾቹ አስተዋውቋል፣ 5ኛ ተከሣሽን የግንባሩ ወታደራዊ ክንፍ አባል እንደሆን ለ2ኛ ምስክር አስተዋውቋል፣ ሲል መግለፁ በፍጹም እውነት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ........ ቀን ........

አይደለም፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የምስክሮቹን ቃል ይመልከትልኝ ምስክሮቹ እኔን የፖለቲካ ድርጅት አባል አለመሆኔ ስላልመሰከሩብኝ ከግንባሩ ጋር የሚያይዘኝ ምክንያት የለም። የ0 ቃቢ. ሕግ 1ኛ ምስክር ዶክተር ሰለሞን አበበ በ1987 ብዙ ጊዜ ከዶክተር ታዬ፣ ከአቶ ስለሺ ብርሃኔ ከአቶ ገ/ፃዲቅ ኃ/ማርያም ከአቶ አበበ ደስታ ጋር እየተገናኘን እንወያያለን፣ አልፎ አልፎ ከአቶ ዮሴፍ ጋር እንገናኝ ነበር፣ ያለ ሲሆን የ0 ቃቢ. ሕግ 2ኛ ምስክር ግን በ1988ዓ/ም መጀመሪያ ከዶክተር ታዬ መተዋወቁን፣ የተዋወቃቸውም ራሱ መሆኑን የገለፀ ነው፣ በዚህ ነጥብ ሁለቱም ምስክሮች መለያየታቸውን ፍ/ቤቱ ይገንዘብልኝ፣ እንዲሁም 1ኛው ምስክር ለፖሊስ የሰጠውና ፍ/ቤት ቀርቦ የመሰከረው ቃል የተለያየ ነው፤ 2ኛው ምስክር ኢብአጌ የተባለው ሕቡዕ የፖለቲካ ድርጅት አባልነቱን የገለፀልን መሆኑን አላስረዳም፣ በውሸት ስም ከሰዎች እንደሚተዋወቅ እንጂ ወንጀል ለመፈጸም የሚፈልግ መሆኑን ነገረኝ የተባበርኩት መሆኑን አላስረዳም የ0 ቃቢ. ሕግ በኔ አስፈጻሚነት በአማሪካ እርዳታ ድርጅቱ ላይ ቦንብ እንዲጣል ስለመደረጉ ያቀረበው በማስረጃ አልተደገፈም፣ በዚህ ክስ ከፍተኛ ፍ/ቤት ወንጀሉን ፈጽመሃል ያለኝ 2ኛው ምስክር ለኦፕሬሽኑ የሚያስፈልግ ገንዘብ አቶ ገብረፃዲቅ ኃ/ማርያም ሰጥቶኛል በማለቱ ብቻ ነው፣ ይህ ምስክር አንዴ የገንዘቡን መጠን አላውቅም፣ ሲል ሌላ ጊዜ ብር 500 ነው ብሏል፣ ሌላ የመሠከረብኝ ሰው የለም። የምስክሩ ቃል ደግሞ በቅራኔ የተሞላ ነው፣ ታፍነው የታሰሩ ሰዎችን በሚመለከት የቀረበው ክስ በቀረበው ማስረጃ መሠረት የተፈጸመው በ2ኛው የ0 ቃቢ. ሕግ ምስክር በመሆኑ የሚመለከተኝ አይደለም፣ 2ኛው ምስክር ሁለቱን ጣለያኖች ያገቷቸው በስለሽ ብርሃኔ ትዕዛዝ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ቃሉን ለውጦ በእኔ ትዕዛዝ ድርጊቱ እንደተፈጸመ ተነግሯል፣ በመሆኑ ምስክርነቱ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፣ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሠጠው ብይን 3ኛ ተከሳሽ አባል ባይሆንም ድርጅቱን በብዙ ጉዳይ ያማክር ስለነበር የ0 ቃቢ. ሕግ 1ኛና 2ኛ ምስክሮች በግልፅ መስክረዋል ያለው ሀሰት ስለሆነ የ2ቱ ምስክሮች ቃል ይታይልኝ፣ 2ኛ ምስክር ማዕከላዊ ምርመራ የሰጠውን ቃል ፍ/ቤቱ ቢመለከት ምስክርነቱ እውነት አለመሆኑን ሊረዳው ይችላል፣ እኔ የኢብአግ አባል አለመሆኔን የ0 ቃቤ ሕግ 1ኛ እና 2ኛ ምስክሮች ገልጸዋል፣ ይህ ከሆነ ከኢብአግ አመራር ተቀብየ 2ኛ ምስክር ድርጊቱን እንዲፈጸም ትዕዛዝ መስጠት ስለማይችል መስክርነቱ የማይታመን በመሆኑ ውድቅ ይደረግልኝ፣ 1ኛው ምስክርም ለፖሊስ የሰጠው ቃልና ፍ/ቤት ቀርቦ የመሰከረው የተለያየና አፉ ላይ የመጣለትን ከመናገር በቀር እውነቱንና የሚያውቀውን ያላስረዳ ስለሆነ ምስክርነቱ በጠቅላላው ውድቅ ሊደረግ ይገባል፣ እኔ በክሱ የተገለጸውን ወንጀል በግሌም ሆነ አብረውን ከተከሰሱት ሰዎች ጋር በግብረ አበርነት አልፈጸምኩም፤ በ0 ቃቢ. ሕግ ምስክሮችም አልተመሰከረብኝም፣ 2ኛ ምስክርም ራሱን ሊደርስበት ከሚችል ችግር ለማዳን ሲል ገንዘብ ሰጥቶኛል ሲል የተናገረው የሚታመን አይደለም፣ የ0 ቃቢ. ሕግ ምስክሮችም ማስረጃዋች ስለሆኑ ፍ/ቤቱ በነፃ ያሰናብተኝ፣ ይህም

ፌዴራል ጠቅላይ
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ቀን

ቢታለፍ የተወሰነብኝ ቅጣት እጅግ ከባድ በመሆኑ ቅጣቱ ተቀንሶ እስካሁን የታሰርኩት በቂ ተደርጐ ልሰናበት የሚል ነው።

3ኛው ይግባኝ ባይ መ/አለቃ ጫኔ ታለ ተፈራ ህዳር 28 ቀን 1992 በተጻፈ የይግባኝ ማመልከቻ ወንጀሉን ሊፈፅም ቀርቶ ስለጉዳዩም ምንም እንደማያውቅ፣ በክሱ ላይ የፈጸመው ወንጀል ምን እንደሆነ በውል ተለይቶ እንዳላቀረበ፣ ተፈጸመ የተባለውም ጉዳይ ክስ በቀረበበት የሕግ አንቀጽ ሥር እንደማይካተት፣ ክስ በማስረጃ የተደገፈ ሳይሆን በመንግሥት ላይ ጦርነት ማነሳሳት በሚል ትኩረት ተሰጥቶት መሆኑን፣ የእምነት ቃል የሰጠሁ ተገድጄ መሆኑን፣ የዐቃቢ ሕግ ምስክሮች ነፃና ገለልተኛ ያለመሆናቸውን፣ የመሰከሩትም ራሳቸውን ለማዳን እንደሆነ፣ ምስክሮቹ የግንባሩ አድርጌ ሊጣሩ መሆናቸውን እየገለፁ እምነት የሚጣልበት ምስክርነት ይሠጣሉ መባሉ አግባብ ያለመሆኑን፣ ይግባኝ ባይ በድርጅቱ ውስጥ በማን እንደተመለመልኩና ለስር ያለመግለፁን የምስክሮቹ ቃል ሊታይም በጥርጣሬ የተሞላ መሆኑን፣ የተያዝኩት ወንጀል ስፈጽም ሳይሆን ከባለቤቴ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን ተሳልመን ከየካ ሚካኤል ሲመለሱ በጥይት ተመትቶ መሆኑንና ከነሐሴ ወር 1987ዓ/ም ጀምሮ ከአ/አበባ ውጭ በደሌ ከተማ በንግድ ሥራ ላይ እንደቆየ በመከላከያ ምስክሮች ማሰረዳቱን ዘርዝሮ እንደክሱ የወንጀል ተግባር ስለመፈጸሙ ሳይረጋገጥበት ጥፋተኛ የተባለው የተቀጣው ያላግባብ መሆኑን በመጥቀስ ውሣኔ ተሠርዞ በነፃ እንዲሰናበት አመልክቷል።

ህዳር 29 ቀን 1992ዓ/ም የተጻፈ የይግባኝ ማመልከቻ 4ኛው ይግባኝ ባይ አቶ ታለጌታ ልዑል /ዳኜ/ ኃይለማርያም ያቀረበው ቅሬታ ፍሬ ሃሳብ በክሱ የይግባኝ ባይ ተግባር ወይም የወንጀል ድርሻ በውል ተለይቶ አልተቀመጠም፣ የፈጸምኩት ወንጀልም የለም የዐቃቢ ሕግ 1ኛና 2ኛ ምስክሮች ራሳቸውን ለማዳን የመሰከሩ ሲሆን የተለቀቁትም በተከሳሾች /ይግባኝ ባዮች/ ላይ ለመመስከር ነው፣ 1ኛ ምስክር በጥበቃ ሥር የነበሩ ለመሆናቸው ከተፅዕኖ ነፃ በሆነ ሁኔታ ይመሰክራሉ ተብሎ አይታሰብም፣ ሁለተኛ ምስክርም መንግሥትን ይቅርታ ጠይቆ ተፈታሁ ባይ በመሆኑ ገለልተኛ ምስክር ሊባል አይችልም፤ ምስክርነታቸውም ቢሆን እርስ በርሱ የሚጋጭና የተምታታ በመሆኑ አጣራጣሪ ነው፣ አጣራጣሪ ማስረጃ ተጠቃሚው ተከሳሽ ነው፣ ይህን አጥራጣሪና ደካማ የዐቃቢ ሕግ ማስረጃ በመከላከያ ምስክሮቼ ቃል አስተባብያለሁ፣ ሁለቱም የዐቃቢ ሕግ ምስክሮች የወታደራዊ ክንፍ አባል ነው፣ ከማለት ውጭ ይህ የመሰለ እንቅስቃሴ አድርጓል ወይም ለማድረግ ሞክሯል፣ በሚል የሰጡብኝ ምስክርነት የለም፣ ስለዚህ የእነዚህ ገለልተኛ ያልሆኑ ምስክሮች ቃል በጠራጣሪ የተሞላ ስለሆነ የተላለፈብኝ ፍርድ የጥፋተኝነና የቅጣት ውሣኔ ይሻርልኝ የሚል ነው።

5ኛው ይግባኝ ባይ ሻምበል ሞገስ አሰፋም ህዳር 25 ቀን 1992ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻ በአብዛኛው በ3ኛና 4ኛ ይግባኝ ባዮች የተጠቀሱትን ነጥቦች በማንሳት ቅሬታውን

ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ........ ቀን ........

ያቀረበ ሲሆን ክሱ ይግባኝ ባዩ ምን ወንጀል እንደፈጸመ በግልፅ ያላስቀመጠ፣ በግብረ አበርነት ስለተፈጸመ የወንጀል ድርጊት ወይም ሙከራ ወይም ዝግጅት የተባለ ነገር እንደሌለ ጉዳዩ በጣቢያ የተሠጠውም ቃል ጥርሴ ተሰብሮና አካለ ጉዶሎ ሕይወቴን ለማትረፍ ስለሆነ ተጠያቂ አያደርገኝም በነፃ ሊቀዳ የሰጠሁት ቃል ለመሆኑም የደረጃ ምስክር ቀርቦ አላረጋገጠብኝም፣ ይህ ቃሌ ለውሣኔ መሠረት መደረጉ ያላግባብ ነው፣ ኑርዬ ናዝሬት ሆኖ በእርሻ እንምተዳደርና ዘር ለመግዛት የካቲት 23/88 አ/አበባ መጥቼ መቅረቴን፣ መታሰሬን፣ መደብደቤን፣ በመከላከያ ምስክሮች አስረድቻለሁ፣ የዐቃቢ ሕግን ማስረጃም በዚሁ አላስተባበለም ስለዚህ የቀረበብኝ ክስ በማስረጃ ያልተደገፈ ነው፣ የመከላከያ ምስክሮችም እንደጭብጡ ያስረዱልኝ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሰርዞ በነፃ ልሰናበት ብሏል።

ዓቃቢ ሕግ ይግባኝ ባዮች ላቀረቡት ይግባኝ መልስ እንዲሰጥ ታዝዞ በ17/09/93 እና በ28/9/93ዓ/ም በተጻፈ ማመልከቻዎች መልስ ሰጥቷል፤ ፍሬ ቃሉ የሚከተለው ነው።

የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር እየተባለ የሚጠራው ድርጅት በይግባኝ ባዩችና ግብረአበሮቻቸው የተመሠረተ ለመሆኑ 1ኛ እና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በሰጡት ቃልና በ1ኛ ይግባኝ ባይ በሥር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሣሽ መኖሪያ ቤቶችና ቢሮዎች የተገኙ ሰነዶች በሚገባ ያስረዳሉ። ለድርጅቱ መቋቋም ሃሳብ ያቀረቡት 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር አቶ ቢረሳው ምናሉ /ዩሴፍ/ እንደሆኑ በሥር ፍ/ቤት ምስክርነት የሠጡ ሲሆን በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 35 መሠረትም የእምነት ቃል ሠጥተዋል፤ ምስክሩ ከኅዳር ወር 1985 ዓ.ም ወዲህ በኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር ሥር ሲንቀሳቀሱ የቆዩ መሆኑ፣ ከዚያ በፊት በመኢሕድ አባልነት እንዲጠሩና 2ኛ ይግባኝ ባይ ያበረታቱአቸውና ትዕዛዝም ይሠጧቸው እንደነበረ ገልፀዋል። ድርጅቱ ከ1985-1987 ያልተጠናከረ ስለነበር ማጠናከርና ማዕከል ማቋቋም በማስፈለጉ በጥቅምት ወር 1988 ዓ.ም ስብሰባ ተደርጎ ማዕከላዊ ኮሚቴ መቋቋሙን አስረድተዋል፤ 1ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክርም 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር ባቀረቡት ሃሳብና በእጅ የተፃፈ የፖለቲካ ኘሮግራም መሠረት በመስማማት ድርጅቱን እንደ አዲስ አጠናክረው በማቋቋም 1ኛ ይግባኝ ባይ ሊ/መንበር፣ አቶ ስለሺ ብርሃኔ ም/ሊቀመንበርና ገንዘብ ያዥ፣ 1ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር አባልና የወታደራዊ ክንፍ ኃላፊ በመሆኑ መመደባቸውንና ቃለ መሃላ ፈፅመው መለያየታቸውን አስረድተዋል። ከዚህም በተጨማሪ የድርጅቱን መቋቋም የሚያመለክቱ የፅሑፍ ማስረጃዎች ቀርበዋል ስለዚህ ድርጅቱ በሕቡዕና በሕገ ወጥነት የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት እንጂ በሀሰት በሁለቱ ምስክሮች የተፈጠረ ባለመሆኑ በዚህ በኩል የተነሳው ነጥብ አግባብነት የለውም።

1ኛና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች በወንጀል ተግባሩ ውስጥ ተሣታፊ የነበሩና ድርጊታቸው ስህተት መሆኑን ተረድተው ይቅርታ ጠይቀው ከምርመራ ክፍሉና ከዓቃቤ

ፌዴራል
ፊርማ ቀን

21

ሕጉ ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ በመሆን ስለድርጅቱ የሚያውቁትን የመሠከሩ ናቸው፡፡ የምስክሮቹ ቃል ተደጋገፊና ተመሣሣይ ከመሆን አልፎም በፅሑፍ ማስረጃም የተጠናከረ ስለሆነ የይግባኝ ባዩች ቅሬታ ቀሪ ሊደረግ ይገባል፤ እነዚህ ምስክሮች የግንባሩ መሥራች አባላት የነበሩ በመሆናቸው ስለድርጅቱ በዝርዝር የሚያውቁ ናቸው፤ የምስክርነት ቃላቸውም በሌሎች ምስክሮች፣ በፅሑፍና በኤግዚቢት ተጠናክሮ ተረጋግጧል ስለዚህ በገለልተኛ ምስክር ቃላቸው አልተደገፈም የሚለው ቅሬታ አግባብነት የለውም፤ በ1ኛ ይግባኝ ባይና በሥር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሣሽ ቤትና ቢሮ ብርበራ የተካሄደው በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 32/2/, 33/1//2//3/ መሠረት ስለሆነ ይህን አስመልክቶ የቀረበውም ቅሬታ ተገቢነት የለውም፤ ይግባኝ ባዩች ከመከላከያ ማስረጃዎቻቸው በሕግ ያልተፈቀደ የፖለቲካ ድርጅት ያለመመሥረታቸውን፣ ወይም በሥራ ክፍፍሉ አለመታቀፋቸውን ወይም ለድርጅቱ እንቅስቃሴ የሚውል ሰነድና የጦር መሣሪያ ያለማሠባሠባቸውን ወይም በመንግሥት ላይ ሁከትና ሽብር ለመፍጠር በድርጅቱ አባላት በተደረገው እንቅስቃሴ ያለመሣተፋቸውን አላስረዱም፤ 3ኛ፣ 4ኛ፣ 5ኛ ይግባኝ ባዩች በ1ኛና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ሥር የወታደራዊ ክንፍ አባላት በመሆን ተመልምለውና ተደራጅተው ሲንቀሳቀሱ የነበሩ በመሆናቸው በቀጥታ በግንባሩ ተግባር ሲሳተፉ ነበር፡፡ ይህም በማስረጃ የተረጋገጠባቸው ስለሆነ ቅሬታቸው ተቀባይነት የለውም፤ የ1ኛና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ምስክርነት 4ኛና 5ኛ ይግባኝ ባዩች በሠጡት የእምነት ቃል የተደገፈም ስለሆነ ተቀባይነት የሚያጣበት ምክንያት የለም፤ ይግባኝ ባዩች በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 27/2/ መሠረት የሠጠነው ቃል በኃይል ሥራ የተገኘ ነው ከማለት ውጭ የእምነት ቃሉ ሕጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ በመከላከያ ማስረጃ ባለማስረዳታቸው በዚህም በኩል የቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም፤ ይግባኝ ባዩች የመከላከያ ማስረጃዎች አቅርበው ያሰሙ ቢሆንም በዓቃቤ ሕግ ማስረጃ የተረጋገጠባቸውን የወንጀል ተግባር ስላላስተባበሉ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ ፍርዱ ሳይለወጥ እንደ ይግባኝ ባዩች የወንጀል ተግባር ተሳትፎ መጠን ቅጣት ይወሰንባቸው የሚል ነው፡፡

ይግባኝ ባዮች በየግላቸው ሰኔ 14 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልስ የይግባኝ ቅሬታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ የተመለከተው ሲሆን መዝገቡ ሲመረመር የ1ኛው ይግባኝ ባይ ዶክተር ታየ ወ/ሰማያት ጠበቃ የሥር ፍ/ቤት ደንበኛዬን ጥፋተኛ ያደረገበት ፅሁፍ በይግባኝ ባዩ የተፃፈ አይደለም፤ ፖሊስ በማመሣከሪያነት የተጠቀሙበት ፅሑፍም ከየት እንደተገኘ አይታወቅም በማለቱና በቴክኒክ ምርመራ ውጤቱ ላይ የማመሣከሪያ ጽሑፍ በይግባኝ ባይ የተፃፉ ለመሆኑ ባለመመልከቱ ይህንን ቅሬታ እንደገና ማጣራቱ አስፈልጓል በዚህ መሠረትም ለማመሣከሪያነት የሚሆኑ የ1ኛ ይግባኝ ባይን የእጅ ፅሑፎች ማግኘት ይቻል ዘንድ ቀድሞ ይሠራበት የነበረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጠይቆ ይግባኝ

ፌዴራል ጠቅላይ ... ትክክለኛ ግልባጭ ... ፊርማ ... ቀን

ባዩ ለዩኒቨርሲቲው የካቲት 28 ቀን 1982 ዓ.ም እና ሐምሌ 4 ቀን 1983 ዓ.ም የፃፋቸውን ሁለት ደብዳቤዎች ልኳል:: ደብዳቤዎቹ በይግባኝ ባዩ ለመፃፋቸው ሁሉ በችሎት እንዲያረጋግጥ ከተደረገ በኋላም እነዚህን ደብዳቤዎችና ዓቃቤ ሕግ በፅሑፍ ማስረጃነት ያቀረበውን ለXYZ ጽ/ቤት በሚል በተፃፈው ጽሑፍ 3ኛ ገፅ ጀርባ ላይ ያለውን የእጅ ፅሑፍ በማያያዝ ለፌዴራል ፖሊስ የቴክኒክ ማስረጃዎች ስብስብና ምርመራ ዋና ክፍል በመላክ የእጅ ፅሑፍ የ1ኛው ይግባኝ ባይ መሆን ያለመሆኑ እንደገና እንዲመረመር ተደርጓል፤ ውጤቱም በ28/5/94 በተፃፈ ሸኚ ደብዳቤ ለዚህ ፍ/ቤት ደርሷል::

ይግባኝ ባዩች በሕግ የተቋቋመ መንግሥትን በኃይል ለመጣል በሕግ ዕውቅና ያላገኘና የታጠቀ የፖለቲካ ድርጅት አቋቁመው የጦር መሣሪያ በያዘ የሽብር ፈጠራ ቡድን ውስጥ መሪና አባል በመሆን በአገሪቱ ውስጥ ለሽብር ፈጠራና ሁከት አድራጎት ተነስተዋል ተብለው በወ/መ/ሕግ ቁጥር 32/1//ሀ/ እና 252 /1//ሀ/ ሥር ተከሰው በዚሁ የሕግ አንቀጽ ጥፋተኞች ተደርገው ቅጣት ተወስኖባቸዋል::

እኛም ይግባኝ ባዩች የወንጀል ድርጊቱን መፈፀማቸውና የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር በተባለው ድርጅት ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው መሆኑ በማስረጃ ተረጋግጧል አልተረጋገጠም? ተሳትፎ ነበራቸው ቢባልስ ድርጊታቸው ሊሸፈን የሚገባው ክስ በቀረበበትና ጥፋተኞች በተደረጉበት የሕግ አንቀጽ ሥር ነው ወይንስ አይደለም የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ከማስረጃዎቹ አንፃር እንደሚከተለው መርምረናል::

በዚህ ክስ ዋነኞቹ የዓቃቤ ሕግ ማስረጃዎች 1ኛ እና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ሲሆኑ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር /ኢብአግ/ አባላት መሆናቸውን ገልፀው ይግባኝ ባዩች ከዚህ ግንባር ጋር ነበራቸው ያሉትን ግንኙነት ዘርዝረዋል::

1ኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክር ከገለፀው ውስጥ በ1987 ዓ.ም ከ1ኛው ይግባኝ፣ ባይ በሥር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ ከነበረው ሟች እና 3ኛ ተከሣሽ ከነበረው ያሁን 2ኛ ይግባኝ ባይ ጋር ስለሀገር ሁኔታ፣ ስለአስተዳደር ጉድለት እየተገናኙ ይነጋገሩ እንደነበረ በኋላም በ1988 ዓ.ም ዩሴፍ የተባለ ሰው /2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር/ በጎቡዕ የተቋቋመ አንድ ኃይል መኖሩንና አመራር ሰጪና ትንሽ እርዳታ እንደሚፈልጉ እንደነገራቸው፣ ዕርዳኑን ማዕ ከል ሁኑን እንዳላቸው፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት ግንባር በሚል በእጅ የተፃፈ መመሪያና ደንብም በግዩን ሆቴል 1ኛ ይግባኝ ባይና ሟች 2ኛ ተከሣሽ ባሉበት እንደሠጣቸው፣ መመሪያና ደንቡን ማጥናት መጀመራቸውን፣ ዩሴፍ ማዕከል ሁኑን ያላቸውን በመቀበል የሥራ ክፍፍል አድርገው 1ኛ ይግባኝ ባይ ሊቀመንበር፣ ስለሺ ብርሃኔ የተባለው ም/ሊቀመንበር 2ኛ ተከሣሽ የነበረው ሟች አቶ ከበደ ደስታ ዋና ፀሐፊ፣ ራሱ 1ኛው ምስክር አባልና የወታደራዊ ክንፍ አገናኝ፣ ዩሴፍ የተባለው ደግሞ አባልና የወታደራዊ ክንፍ ተጠሪ መሆናቸውን፣ በየጊዜውም በተለያዩ ቦታዎች እየተሰባሰቡ ሥራ መቀጠላቸውን፣ ድርጅቱን /ግንባሩን/ ለማጠናከር ከሀገር ውስጥና ውጭ ያሉ ደጋፊዎችን

ፌዴራል ...
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ... ቀን

24

በመውሰድ ለግንባሩ የገቢ ምንጭ ማዳበር፣ የዲፕሎማቲክ ግፊት ለማግኘት የውጭ ዜጎችን ማግኘት እንደነበረ፣ እንዲገደሉ ተወስኖባቸው ከነበሩት ውስጥ ፕሮፌሰር እንድሪያስ እሸቴ፣ አቶ ዳዊት ዩሐንስ፣ ዶክተር አብዱልመጅድ ሁሴን፣ ዶክተር ዱሪ መሐመድ፣ አቶ ክፍሌ ወዳጆ የተባሉት መሆናቸውን እንደሚያውቅ፣ ባንክ ለመዝረፍም ዕቅድ እንደነበራቸው፣ በ1987 ዓ.ም ሁለት ፈረንጆች መታገታቸውንና በአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ጽ/ቤት ላይም ቦንብ እንዲፈነዳ መደረጉን ፍንዳታው የተካሄደው የግንባሩ ማዕከላዊ ኮሚቴ ከመቋቋሙ በፊት እንደሆነ፣ 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ይግባኝ ባዮች በወታደራዊ ክንፍ የተደራጁ የግንባሩ አባላት መሆናቸውን፣ 2ኛ ይግባኝ ባይን በአሜሪካኖች ላይ ለሚወሰደው እርምጃ ለመንቀሳቀሻና ለመሣሪያ መግዣ የሚሆን ገንዘብ እንዲሠጠው ጠይቆት ለዚሁ ተግባር የሚውል ብር 500 እንደሠጠው፣ በግሉም እንደሚረዳው ገልጿል፡፡ ከዚህም ሌላ በ1985 ዓ.ም የተቋቋመውንና በ1988 ማዕከላዊ ኮሚቴው ለተመሠረተው ግንባር ግንኙነት የፈጠረው እሱ መሆኑንና ለዚህ ግንኙነት ደግሞ 2ኛው ይግባኝ ባይ አስተዋጽኦ እንደነበረው መስክሯል፡፡ 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ይግባኝ ባዮችን በሚመለከት በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት 4ኛውን ይግባኝ ባይ የሚያውቀው አንድ ቀን ብቻ እንደሆነ ገልጾ በመቀጠልም 3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ይግባኝ ባዮች ከግንባሩ ጋር እንቅስቃሴ የጀመሩት በ1987 ዓ.ም ነው ብሏል፡፡

ሌሎች የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች የ1ኛ ይግባኝ ባይ ቤትና ቢሮ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሲበረበር የነበሩ፣ 2ኛ ተከሳሽ የነበረው ሟች አቶ ከበደ ደስታ ቤት ሲበረበር የነበሩ፣ ጥይቶችና መሣሪያዎች የተቀመጡበትን ቤቶች ፈትሸው መሣሪያዎቹን ያገኙ የፖሊስ ባልደረቦች በዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ ጽ/ቤት የደረሰውን ፍንዳታ በተመለከተ የመሠከሩ፣ እንዲሁም 3ኛ ይግባኝ ባይ መቶአለቃ ጫኔ ታለ የተያዘበትን ሁኔታ የመሠከሩ ናቸው፡፡

የፅሑፍ ማስረጃዎቹም የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር የተባለውን ድርጅት የሚመለከቱ በ1ኛው ይግባኝ ባይ ቤትና ቢሮ፣ እንዲሁም በሟች በ2ኛው ተከሣሽ ቤት የተገኙ የተለያዩ ፅሑፎች ናቸው፡፡ የፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ውጤትም ቀርቧል፤ 3ኛውና 5ኛው ይግባኝ ባዮች ለፖሊስ የሠጡት የተከሳሽነት ቃልም የፅሑፍ ማስረጃው አካል ነው፡፡

ከፍ ሲል ዋና ዋና የምስክርነት ቃላቸው የሠፈረው 1ኛ እና 2ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ራሳቸውም ሆነ ይግባኝ ባዮች የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር ከተባለው ድርጅት ውስጥ የነበራቸውን ተሳትፎ ገልፀዋል፡፡

1ኛው ይግባኝ ባይ ይህንን ግንባር ለማጠናከር በ2ኛው ምስክር በኩል የቀረበውን ጥያቄ በመቀበል ከምስክሮቹ፣ በከፍተኛ ፍ/ቤት 2ኛ ተከሳሽ ከነበረው ሟች አቶ ከበደ ደስታና አቶ ስለሺ ብርሃኔ ከተባሉት ጋር በመሆን በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ቦታዎች ስብሰባ አድርገው ግንባሩን ስለሚያጠናክሩበት፣ ገንዘብ ስለሚገኝበት መንገድ፣ እርምጃ ስለሚወስድባቸው ግለሰቦች፣ የጦር መሣሪያ ስለሚገኝበት ሁኔታ ይመክር እንደነበር ተመስክሯል፡፡ ግንባሩን ለማጠናከር በተደረገ የሥራ ክፍፍልም ምንም እንኳን በመሪነት

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ድ ቤት
ፊርማ

በተለየ ሁኔታ ፊፅሟል ተብሎ የተነገረበት ነገር ባይኖርም ሊቀመንበር ተደርጎ መመረጡ ተነግሯል፡፡ በስብሰባቸው ላይ ለግንባሩ መዋጮ ሊሠጡ የሚችሉ ሀብታሞች የስም ዝርዝር እንደተፃፈ በ1ኛው ምስክር የተገለፀ ሲሆን "የወያኔ"፣ "የደርግ ሀብታም"፣ "With Warning 10,000" የሚል ለXYZ ጽ/ቤት በሚለው ፅሑፍ 3ኛ ገፅ ጀርባ ላይ የሠፈረው የሀብታሞች ስም ዝርዝር የተፃፈበት የእጅ ፅሑፍ የ1ኛው ይግባኝ ባይ መሆኑ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ፅሑፍ በጀርባው የተፃፈበት ሰነድም ለXYZ ጽ/ቤት በሚል በግንባሩ ወታደራዊ ክንፍ የተዘጋጀ የግንባሩ ወታደራዊ ክንፍ የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅዶች የተገለፀበት ነው፡፡

ግንባሩን የሚመለከቱ ፅሑፎች ከ1ኛው ይግባኝ ባይ ቤትና ቢሮ መገኘታቸውም ታውቋል፤ እነዚህ ፅሑፎች በይግባኝ ባይ ቤትና ቢሮ መገኘታቸው ብቻውን ይግባኝ ባዩ ከግንባሩ ጋር ስለነበረው ሕገ ወጥ ግንኙነት አያስረዳም ሊባል ይችላል፤ ከላይ በምስክሮቹ ከተገለፀውና በይግባኝ ባዩ መፃፉ ከተረጋገጠው ፅሑፍ ጋር በአንድነት ሊገናዘብ እንዲሁም ተመሳሳይ ፅሑፍ ጋር በአንድነት ሊገናዘብ እንዲሁም ተመሳሳይ ፅሑፎች በሥር ፍ/ቤት 2ኛ ተከሣሽ ከነበረው ሚች ቤት መገኘታቸው ሲታይ 1ኛ ይግባኝ ባይ ከግንባሩ ጋር ግንኙነት እንደነበረው የሚያሳዩ ናቸው፡፡

እነዚህ ከ1ኛው ይግባኝ ባይ ቤትና ቢሮ የተገኙ ፅሑፎች እርሱ በሌለበት ተገኙ የተባሉ ስለሆነ ተቀባይነት የላቸውም የሚል ክርክር ቀርቧል፡፡ ፍተሻው በፍ/ቤት ትዕዛዝ ታዛቢዎች በተገኙበት የተካሄደ በመሆኑ ይግባኝ ባይ በወቅቱ ስላልነበረ ብቻ የተገኙት ፅሑፎች /ሰነዶች/ የይግባኝ ባይ ጠበቃ እንዳለው የፈጠራ ሰነዶች ናቸው ማለት አይችልም፡፡ የፈጠራ ሰነዶች ስለመሆናቸው የቀረበ አንዳችም የመከላከያ ማስረጃ የለም፡፡

የዓቃቤ ሕግ ምስክሮችን ቃል ለማስተባበል የ1ኛ ይግባኝ ባይ መከላከያ ምስክሮች ተሰምተዋል፡፡ 1ኛው ምስክር ዶክተር ቀኛዝማች ሰለሞን አበበ /1ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር/ ባቀረበለት ጥያቄ መሠረት ይግባኝ ባዩ በግንባሩ ውስጥ አባል እንዲሆን አነጋግሮት ፈቃደኛ ያለመሆኑን ገልጿል፡፡ ነገር ግን ተሳትፎውን አስመልክቶ በሁለቱ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች፣ በፖሊስ የቴክኒክ ምርመራ ውጤቱና በብርበራ በተገኙት ፅሑፎች የተመለከቱትን የሚያስተባብል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሁለተኛዋ የ1ኛ ይግባኝ ባይ መከላከያ ምስክር የተለያዩ ፅሑፎች ከይግባኝ ባዩ ቤት በብርበራ ሲያዙ የተገኘች መሆኗንና በያንዳንዱ ፅሑፍ ላይ ያለመፈረሟን፣ ነገር ግን በወቅቱ በተያዘው የሰነዶች ዝርዝር ላይ መፈረሟን ገልፃለች፡፡ በይግባኝ ባዩ ላይ በማስረጃነት የቀረቡት ሰነዶች ከይግባኝ ባዩ ቤትና ቢሮ በዝርዝር ከተያዙት ውጭ የሆኑ ናቸው ስላልተባለ በሰነዶቹ ላይ ያለመፈረሟ ሰነዶቹ /ማስረጃዎቹ/ ከይግባኝ ባዩ ቤት የተገኙ አይደሉም የሚል ጥርጣሬን ለማንሳት የሚያስችል አይሆንም፡፡ በፈረመችበት ዝርዝር ላይም የፈረመችው አላነበብኩም በማለቱ ብቻ በሥፍራው የነበሩ የዓቃቤ ሕግ ምስክሮች ሆነው

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ........ ቀን ........

የቀረቡ ታዛቢዎች ያስረዱትን የሚያፈርስና ብርበራው የማይታመን ነው የሚያሰኝ አይሆንም፡፡ ብርበራው ሲካሄድ በቦታው የነበሩ የቀበሌና የፖሊስ አባላት በሙሉ ያልተገኘን ማስረጃ በሀሰት ተገኘ ብለው የመሠከሩ እንደሆነ ተደርጎ መቅረቡ በተጨባጭ ማስረጃ ያልተደገፈ ጭፍን ክርክር ነው፡፡

ለXYZ በሚለው ፅሑፍ 3ኛው ገጽ ጀርባ ላይ የሠፈረው የእጅ ፅሑፍ የ1ኛው ይግባኝ ባይ መሆኑ ተረጋግጧል ሲል የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ የጠቀሰውን ይግባኝ ባይ በመቃወሙና አንድ የቅሬታ ነጥብ በማድረጉ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ፅሑፉ እንደገና እንዲመረመር ተደርጎ በ1ኛው ይግባኝ ባይ የተፃፈ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለሆነም በዚህ ረገድ የይግባኝ ባይ ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ 1ኛ የዓቃቤ ሕግ ምስክር የሀብታሞችን ዝርዝር 2ኛው ይግባኝ ባይ የፃፈ ይመስለኛል፣ የኔም ሊኖር ይችላል ሲል መግለፁ በቴክኒክ ምርመራ ከተገለፀው ጋር የሚጋጭ ሆኖ አይታይም፡፡ ምክንያቱም ምስክሩ እንደገለፀው አባላቱ የሀብታም ዝርዝር ይፅፉ የነበረው የሚያውቁትን ያህል ስለሆነ ከሁለቱ ሰዎች በቀር የፃፈ ሰው አልነበረም ወደሚል ድምዳሜ ስለማያደርስ ነው፡፡ ምስክሩ ዝርዝሩን የፃፉትን ሰዎች በእርግጠኝነት ሳይሆን "ይመስለኛል" "ሊኖር ይችላል" በሚል መግለፁም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ በመሆኑም ፅሑፉ የዶክተር ታዬ አይደለም መባሉም አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሁለተኛ ይግባኝ ባይን በሚመለከት 1ኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክር የገለፀው ይግባኝ ባዩ የግንባሩ አባል ባይሆንም ከግንባሩ አባላት እንደማይለዩ፣ ችግራቸውን በሚመለከት በተለይም አዲስ አበባ ውስጥ ማን ገንዘብ ሊሠጣቸው እንደሚችል ይጠይቁትና ያማክሩት እንደነበር፣ በስብሰባቸው ላይ ግን እንደማይገኝ፣ ዩሲፍ የተባለውን የግንባሩን አባል ያገናኘው ይኸው 2ኛ ይግባኝ ባይ መሆኑን፣ ግንባሩ ኅቡዕ ቢሆንም ይግባኝ ባዩ ከግንባሩ አባላት ጋር እንደሚተዋወቅ፣ የግንባሩ አባል ግን ሊያደርጉት በራሳቸው ምክንያት እንዳልፈለጉ ነው፡፡

2ኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክር በበኩሉ በመጀመሪያ የተገናኘነው ከ2ኛው ይግባኝ ባይ ጋር መሆኑን በእሱም አማካኝነት ከ1ኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክርና ስለሺ ብርሃኔ ከተባለው የግንባሩ አባል ጋር እንደተዋወቀ፣ ከ2ኛው ይግባኝ ባይ የተዋወቀው የግል ችግሩን በመግለጽ እንደነበረ፣ በኋላ ላይም በግንባሩ ሊወሰዱ ለታቀዱ እርምጃዎች ለኦፕሬሽን የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች ለመግዛት ከዚህ ይግባኝ ባይ ገንዘብ መውሰዱን ይህም በአሜሪካኖች ላይ ለሚወሰደው እርምጃ መንቀሳቀሻ እና መሣሪያ ወግዣ ብሎ ምሥክር ጠይቆት ብር 500/አምስት መቶ ብር/ መሆኑን ገልጿል፡፡

የእነዚህ ሁለት ምሥክሮች ምሥክርነት ለማስተባበል ይግባኝ ባይ ምሥክሮቹ ለፖሊስ የሠጠውን ቃል እንዲታይለት የፖሊስ የምርመራ መዝገብ እንዲቀርብለት ከመጠየቅ ውጭያቀረበው የመከላከያ ማስረጃ የለም፡፡ሁለቱ ምሥክሮች የግንባሩ አባላትና የወንጀሉ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ........ ቀን ........

27

ዋና ተዋናዮች በመሆናቸው በእኔ ላይ የሠጡት ምሥክርነት ሊታመን አይገባም፣ በፍርድ ቤት የሠጡት ቃል ለፖሊስ ከሠጡት ቃል የተለየ ነው የሚል ቅሬታ አቅርቧል፡፡

በመሠረቱ ዓቃቤ ሕግ በአንድ የወንጀል ተግባር ከሌሎች ሰዎች ጋር ተሳትፎ የነበረውን ሰው ከመክሰስ ይልቅ በማስረጃነት ቢቆጥረው የሚከለክለው የሕግ ድንጋጌ የለም ይግባኝ ባዮች የተከሰሱበትን ዓይነት ወንጀሎች በማስረጃ ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ከመሆኑ አንፃር ከወንጀሉ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ምሥክር ቢጠፋ ተከሣሽ ሊሆን ይችል የነበረን ሰው ምሥክር ማድረግ ዓቃቤ ሕጉ ቢያንስ ከብዙዎች ወንጀል ፈፃሚዎች የተወሰኑት ለፍርድ እንዲቀርቡ የሚጠቀምበት በመሆኑ አዲስ አሠራር አይደለም፡፡

በዚህ ጉዳይ ቀርበው የመሠከሩት ምስክሮች ምሥክርነታቸው ሀሰተኛ ወየም ከሕግ አግባብ ውጭ የተገኘ ለመሆኑ በተጨባጭ እስካልተረጋገጠ ድረስ በግንባሩ ሕገወጥ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው በመሆኑ ብቻ ሊታመኑ አይችልም ማለት አይቻልም፡፡ የሠጡት ምሥክርነት ሳይስተባበል በደፈናው ዋጋ ሊሠጠው የማይገባ ነው መባሉም ተቀባይነት የለውም፡፡

እነዚህ ምሥክሮች ለፍርድ ቤት የሠጡት ምሥክርነት የማይታመን መሆኑን ለማስረዳት እንዲቀርብ የተጠየቀውን የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ቀርቦ አስቀርበን ተመልክተናል፡፡ በመሠረቱ ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ የሠጠው የዓቅቤ ሕግ ምሥክሮች ለፍርድ ቤት የሠጡትን ምሥክርነት መሠረት በማድረግ እንጂ በፖሊስ ጣቢያ ቃላቸው መሠረት አይደለም፡፡ የ2ኛ ይግባኝ ባይ ጠበቃ ቅሬታ ግን ያተኮረው የዐቃቤ ሕግ ማስረጃ ሆኖ ባልቀረበ ለፖሊስ ምርመራ መዝገብ ላይ ምስክሮች ወጡ በተባለው የምሥክርነት ቃል ላይ ነው፡፡

ምሥክሮቹ ለፍርድ ቤት የሠጡት ቃል የበለጠ የሚታመን መሆኑ አይካድም ያም ሆኖ ግን ለፖሊስ በሠጠው ቃልም ፍ/ቤት የሠጡትን ቃል በሚቃረን መልኩ የመሠከሩ በመሠረታዊ ነጥቦች ላይ ልዩነት የሚታይበት ምሥክርነት የሠጡ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ልዩነት ቢኖር ለፖሊስ የሠጡት ቃል በጣም ዝርዝር ያለ መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው የዓቃቤ ሕግ ምሥክር ለፖሊስ በሠጠው ቃል በ2ኛው ይግባኝ ባይ ትዕዛዝ አድራሽነት ይፈፅም የነበረመሆኑን መግለፁን ፍ/ቤት ሲቀርብ ያለማንሳቱና ለኦፕሬሽኑ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከይግባኝ ባይራሱ ጠይቆ መውሰዱን መናገሩ ይግባኝ ባይ ለግንባሩ ሕገወጥ ዓላማ ማስፈፀሚያ ዕርዳታ ማድረጉን በሚመለከት በምስክርነቱ የሚታዩ መሠረታዉ ልዩነት የለም፡፡ መሠረታዊ ያለሆኑ ልዩነቶች ደግሞ ምሥክርነቱን የማይታመን ነው የሚያሰኙ አይሆኑም፡፡

2ኛው ይግባኝ ባይ የግንባሩን አባላት ያማክር ነበር አይለየንም ተብሎ በ1ኛው የዐቃቤ ሕግ ምሥክር የተነገረ መሆኑን የከፍተኛው ፍ/ቤት መዝገብ ስለሚያሳይ የሥር ፍ/ቤት ያልተመሠከረ ነገር ጠቅሶ ጥፋተኛ አደረገኝ የሚለው ክርክርም ተገቢ አይደለም፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ቀን ........

ሁለቱ ምሥክሮች ፍርድ ቤት ቀርበው ምሥክርነት የሠጡት ተገድደውና በተፅዕኖ ሥር ሆነው ነው የሚልም ክርክርቀርቧል። በተለይ 2ኛው ይግባኝ ባይ 2ኛው የዐቃቤ ሕግ ምሥክር የመሠከረው ተደብድቦና በተፅዕኖ ሥር ሆኖ መሆኑን ለማስረዳት ጠይቄ ተከልክያለሁ ብሏል። ምሥክሮቹ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኛ ግንባር አባላት የነበሩና መንግሥት ይቅርታ ጠየቀው መለቀቃቸውንና ቃላቸውን የሠጡትም በፈቃዳቸው መሆኑን ለፍ/ቤት ገልፀዋል። ምሥክሮቹ ፍ/ቤት ቀርበው ይህን በመሠከሩበት ወቅት የ2ኛው ይግባኝ ባይ ጠበቃ 2ኛው ምሥክር ተገዶ የመሠከረ ወይም ሀሰት የተናገረ መሆኑን በሚመለከት በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት ያነሳው አንድም ጥያቄ አልነበረም። ይህ ምሥክር በ1ኛው ይግባኝ ባይ ጠበቃ መስቀለኛ ጥያቄ በዚህ ጉዳይ ታስሮ በራሱ አነሳሽነት ይቅርታ ጠይቆ መፈታቱን አስርድቷል። 2ኛው ይግባኝ ባይ ጠበቃም ምሥክርነቱን ለማፍረስ ወይም ጥርጣሬላይ ለመጣል ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በመስቀለኛ ጥያቄ ተገቢውን ማጣራት ማድረግ በቻለ ነበር። ይህንን ሳያደርግ ቀርቶ ምስክሩ ፍ/ቤት ቀርቦ በመሃላ ቃል ሥር ሆኖ የሠጠውን ምሥክርነት ፍ/ቤት ቀርቦ የሠጠው ምሥክርነት ተገድዶ ለመሆኑ በሌሎች ተከሣሾች ምስክርነት ላስረዳ በማለት የቀረበውን ጥያቄ ፍ/ቤቱ ያልመቀበሉ የሚነቀፍ አይደለም።

ለማጠቃለልም 1ኛው ይግባኝ ባይ ዶክተር ታየ ወ/ሰማያት የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር በተባለው ድርድት ውስጥ ግንባሩን ለማጠናከር የቀረበውን ጥያቄ በመቀበል በሕገወጥ የግንባሩ ዓላማዎች ተሳትፎ የነበረው ለመሆኑ በዓቃቤ ሕጉ የሰውና የፅሁፍ ማስረጃዎች በመረጋገጡ 2ኛው ይግባኝ ባይ አቶ ገ/ጻድቅ ኃ/ማርያም የዚሁ ሕገወጥ ግንባር አባላት ያማክርና በዩ ኤስ ኤ ኢይ ዲ በተባለ የአሜሪካን ድርጅት ላይ ግንባሩ ላደርሰው የቦንብ ፍንዳታ የገንዘብ ዕርዳታ ማድረጉ በመመስከሩ የተሳትፏቸውን ደረጃ ወደ ኋላ ላይ የምንመለስበት ቢሆንም ከተጠያቂነት ግን የሚድኑ ሆነው አልተገኙም።

3ኛ፣ 4ኛና 5ኛ ይግባኝ ባዮች የግንባሩ የወታደራዊ ክንፍ አባላት ናቸው። በሚል የተከሰሱ ሲሆኑ የቀረቡባቸውን ማስረጃዎች አንድ በአንድ መርምረናል፡

1ኛው የዐቃቤ ሕግ ምሥክር እነዚህን ይግባኝ ባዮች ዮሴፍ /2ኛ የዐቃቤ ሕግ ምሥክር/ የግንባሩ ወታደራዊ ክንፍ አባላት ናቸው ብሎ እንዳስተዋው ያገኛቸውም በመንገድ ላይ በአንድነት እንደሆነ ገልፆ በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት ደግሞ የተዋወቃቸው በተናጠል መሆኑን ተናግሯል።

ዮሴፍ የተባለው 2ኛው ምሠክር ይግባኝ ባዮችን እንደሚያውቀቸው የግንባሩ አባላትና በመታደራዊ ክንፍ የተደራጁ መሆናቸውን ከ1987ዓ.ም. ጀምሮ ከግንባሩ ጋር እንቅስቃሴ እንደጀመሩመስክሮ በይግባኝ ባዮች መስቀለኛ ጥያቄ 4ኛውን ይግባኝ ባይ የሚያውቀው ለአንድ ቀን ብቻ መሆኑንን በሌላ ቀን ታሞ እንደጠየቀው ገልጿል።

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ......

29

15ኛው የዐቃቤ ሕግ ምሥክር 3ኛው ይግባኝ ባይ እንደሚፈልግ በአለቃው ተነግሮት ይገኝበታል ወደተባለበት መርካቶ አካባቢ በመሄድ ለይግባኝ ባዩ ፖሊስ መሆኑን ነግሮ ትፈለጋለህ ሲለው ከካፖርቱ በሥር ኡዚ መሣሪያ አውጥቶ ተኩሶ እንደመታው የገለፀ ነው።

3ኛውን ይግባኝ ባይ በሚመለከት ሌላው የዓቃቤ ሕግ ማስረጃ ይግባኝ ባዩ ለፖሊስ የሠጠው የተከሣሽነት ቃል ነው።በዚህ ቃሉም ዮሴፍ ከተባለው ሰው ጋር ተዋውቆ በታህሣሥ ወር 1988ዓ.ም. ዮሴፍ ኡዚ መሣሪያ ፈልግልኝ ብሎ እንደነገረው መሣሪያውንም አፈላልጎ አግኝቶ ብር 850 ከዮሴፍ ተቀብሎ ገዝቶ እንዲሠጠው ሌላ አንድ ተጨማሪ ኡዚ እንደሚፈልግ ነግሮት ብር 850 እንደሠጠው አሮጌ ኡዚ ገዝቶ ዮሴእ አስቀምጥልኝ ስላለው ማስቀመጡን የእጅ ቦምብም አስቀምጥልኝ ስላለው አስቀምጦለት ሳለ በኋላ የተያዘበት መሆኑን በአጠቃላይ ለመሣሪያ መግዣ ብሎ ዮሴፍ ብር 2000 እንደሠጠው ዮሴፍ ዕቃ አመላለስበታለሁ የተለያዩ ቦታዎች እሄድበታለሁ ስለላቸው ከጓደኛው ጋር ሆነው መኪና የተከራዩለት መሆኑን በኋላም ጓደኛው መኪናዋን መመለስ አለብን ዬሴፍ በኅቡዕ ለሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት አስተዋውቃቸኋለሁ ብለናል ስላለውና ዮሴፍ የሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ከእነርሱ ድብቅ በመሆናቸው ችግር ይደርስብናል በማለት ሁለተኛ መኪና አንከራይልህም እንዳሉት የተግባባሽን ለተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ አንፈልግም ሲሉት ይግባኝ ባዩን አንተ ዘንድ ያለኝን አንድ ኡዚና አንድ ቦንብ ስጠኝ ብሎ እንደተቆጣው ለመኪና ከራይ መያዣ የተሠጠውን ብር 1000/አንድ ሺህ ብር/ መልስልኝ ያላቸው መሆኑን መሣሪያውን ሊሠጡት ተቀጣጥረው ሲጠብቁት መያዙን መስማታቸውን መሣሪያዎቹን ከገዙበት መልሰው ገንዘቡን ለመውሰድ ሲሉ 3ኛው ይግባኝ ባይ መያዙን የገለፀበትና ዬሴፍ ጎጃም ወስጄ እሸጣለሁ በማለቱና ለአንተም የደላላ እልክልሃለሁ ስላለው መሣራያዎቹን የገዛለት እንጂ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አርበኞች ግንባር ውስጥ እንቅስቃሴ ያላደረገና የማያውቀው ድርጅት መሆኑን ያስረዳበት ነው።

15ኛው ይግባኝ ባይ የተከሣሽንት ቃል በዐቃቤ ሕግ ማስረጃዎች ቀርቧል። በዚህም ይግባኝ ባይ በኢትዮጵያ ብሄራዊ አብረኞች ግንባር ወታደራዊ ክንፍ አባል መሆኑን አባል የሆነውም በመጋቢት ወይም በሚያዚያ ወር 1987ዓ.ም. በዬሴፍ አማካኝነት እንደነበር የገለፁበትን ሌሎች ዝርዝሮችም የተነገረበት ነው።

ዐቃቤ ሕግ በ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ይግባኝ ባዮች ላይ ያቀረባቸው የሰው ምስክሮችና የፅሑፍ ማስረጃዎች ከላይ እንደተመለከተው 1ኛው ምስክር ዩሴፍ ይግባኝ ባዮችን አንድ ላይ ሆነው በመንገድ ተገናኝተን አስተዋወቀኝ ካለ በኋላ ይህን ቃሉን በመለወጥ በተናጠል የተዋወቀችው መሆኑን ገልጿል 3ኛውን ይግባኝ ባይ በሚመለከት ዓቃቤ ሕግ ክሱን ያስረዳልኛል ሲል ያቀረበው የይግባኝ ባይ የተከሳሽነት ቃል ዩሴፍ በኅቡዕ በሚንሰሳቀስ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ አለበት ብሎ ጓደኛው ሲነግረው የቀረብከን ለዚህ ከሆነ አንፈልግም

ፌዴራል ጠቅላይ ...
ትክክል ግልባጭ
ፊርማ ........ ቀን

30

ብለው ይግባኝ ባዩና ጓደኛው የተጣሉት መሆኑን የገለፀበት እንጂ እንደክሱ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር የወታደራዊ ክንፍ አባል መሆኑን ወይም ከግንባሩ ጋር ግንኙነት የነበረው መሆኑን ያመነበት አይደለም፡፡

4ኛው ይግባኝ ባይን የሚያውቀው ለአንድ ቀን ብቻ እንደሆነ የተናገረው 2ኛው ምስክር በኋላ ደግሞ ሦስቱም ይግባኝ ባዮች ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በግንባሩ ወታደራዊ ክንፍ ሥር እንደሚንቀሳቀሱ ገልጿል፡፡ ይህ ምስክር የግንባሩ ወታደራዊ ክንፍ ተጠሪ እንደነበረ የተነገረ ስለሆነ በእርሱ ሥር ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ ይንቀሳቀስ ነበር ያለውን 4ኛ ይግባኝ ባይ ለአንድ ቀን ብቻ ነው የማውቀው ማለቱ አጠራጣሪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በ5ኛው ይግባኝ ባይም ላይ የቀረበቡት የሰው ምስክሮች በ3ኛ እና 4ኛ ይግባኝ ባዮች ላይ የተሰሙት ሲሆኑ በተደጋገፈ ሁኔታ ይግባኝ ባዩ በወታደራዊ ክንፉ ውስጥ ተሳትፎ የነበረው ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡ የተከሳሽነት ቃሉም በሌላ ማስረጃ ያልተደገፈና በነፃ ፈቃዱ የተገኘ እንደነበር በመከላከያ ምስክሮቹ የተገለፀ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡

በእነዚህ ምክንያቶችም 3ኛ ይግባኝ ባይን በሚመለከት የቀረቡት የሰውና የፅሁፍ ማስረጃዎች የማይደጋገፉ ስለሆነ፣ በ4ኛ እና 5ኛ ይግባኝ ባዮች ላይ የቀረቡት ምስክሮችም በዓቃቤ ሕጉ ዋና ጥያቄና በመስቀለኛ ጥያቄ ወቅት የተለያየ በመሆኑ ዓቃቤ ሕግ በ3ኛ፣ 4ኛ እና 5ኛ ይግባኝ ባዮች ላይ ከጥርጣሬ በፀዳ ሁኔታ ክሱን አስረድቶባቸዋል ማለት አልተቻለም፡፡

ስለሆነም በ3ኛ ይግባኝ ባይ መቶ አለቃ ጫኔ ታለ፣ በ4ኛ ይግባኝ ባይ አቶ ታለጌታ ልዑልና በ5ኛ ይግባኝ ባይ ሻምበል ሞገስ አሰፋ ላይ የተሠጠውን የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሠረት በመሠረዝ በነፃ እንዲሰናበቱ ወስነናል፡፡

በመቀጠል 1ኛ ይግባኝ ባይ ዶክተር ታዬ ወ/ሰማያትና 2ኛ ይግባኝ ባይ አቶ ገ/ፃድቅ ኃ/ማርያም በግንባሩ ውስጥ የነበራቸውን የተሳትፎ ደረጃ እንመለከታለን፡፡

ዓቃቤ ሕግ ሁሉንም ይግባኝ ባዮች የከሰሳቸውና የሥር ፍ/ቤትም ጥፋተኞች ያደረጋቸው በወ/መ/ሕግ ቁጥር 32(1)(ሀ) እና 252 (1)(ሀ) ሥር ነው፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር የተባለው ድርጅት የተቋቋመው በ1985 እንደነበር 2ኛው የዓቃቤ ሕግ ምስክር አስረድቷል፡፡ በፅሑፍ ማስረጃነት ዓቃቤ ሕግ ያቀረበው የግንባሩ የፖለቲካ ፕሮግራም ከፊት ሽፋኑ ላይና በመጨረሻው ገጽ የተፃፈው ቀን ኅዳር 1985 ዓ.ም የሚል በመሆኑ የምስክሩን አገላለፅ የሚደግፍ ነው፡፡ 1ኛው ይግባኝ ባይ ከግንባሩ አባላት ጋር የተገናኘው በ1988 ዓ.ም ለመሆኑ በዓቃቤ ሕግ ምስክሮቹ የተገለፀ በመሆኑና ግንባሩም በሌሎች ሰዎች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ በ1985 መመስረቱ ስለታወቀ እንደክሱ ግንባሩን ካቋቋሙት አንዱ 1ኛው ይግባኝ ባይ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ ............ ቀን ............

2ኛው ይግባኝ ባይ በምስክሮቹም እንደተገለፀው የግንባሩ አባል አልነበረም ስለተባለ ግንባሩን አቋቁሟል የሚባል አይደለም።

የወ/መ/ሕግ ቁጥር 252(1)(ሀ) በመንግሥት ወይም በሕገ መንግሥቱ በተቋቋሙት ባለሥልጣኖች ላይ ሕዝቡ የጦር መሣሪያ ይዞ እንዲነሳ በማድረግ ሁከት በማንሳት ወይም የጦር መሣሪያ የያዙ ሽፍቶች በማስነሳት ሽብር ያነሳ ወይም ለማንሳት የፈለገ ሰው ከ5 /አምስት/ ዓመት ፅኑ እሥራት እስከሞት በሚደርስ ቅጣት ሊቀጣ እንደሚችል ይደነግጋል።

በዚህ የሕግ ድንጋጌ ሥር አንድን ተከሳሽ ጥፋተኛ ለማድረግ የወንጀል ተግባሩ እንዲፈፀም የሃሳቡ ጠንሳሽ፣ ዋና አነሳሽና መሪ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ሕዝብ የጦር መሣሪያ ይዞ እንዲነሳ በማድረግ ሁከት በማንሳት፣ ሽብር ያነሳ ወይም ለማንሳት የፈለገ የሚሉት ኃይለ ቃላት የወንጀሉ ተግባር ሃሳብ አመንጪና የድርጊቱን ጀማሪዎች ለማመልከት መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም።

በያዝነው ጉዳይ ይህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አርበኞች ግንባር የተባለውን ሕገ ወጥ ድርጅት መሥራቾችና የሕገ ወጥ ዓላማው ሃሳብ አፍላቂዎች 1ኛ እና 2ኛ ይግባኝ ባዮች ናቸው ተብሎ ማስረጃ አልቀረበም። ግንባሩ ለተቋቋመበት ሕገ ወጥ ዓላማም አነሳሾቹ እነርሱ ለመሆናቸው አልተመሠከረም። 1ኛው ይግባኝ ባይ በ1988 ዓ.ም አስቀድሞ የነበረን ድርጅት ለማጠናከር የቀረበለትን ጥያቄ በመቀበል ሊቀመንበር መሆኑ ብቻውን የወንጀሉ ዋና አነሳሽ የሚያደርገው አይሆንም። ስለሆነም 1ኛ እና 2ኛ ይግባኝ ባዮች በወ/መ/ሕግ ቁጥር 252(1)(ሀ) ሥር ጥፋተኞች መባላቸው አግባብ አይደለም ብለናል።

በሌላ በኩል ግን ከፍ ሲል በዝርዝር ለመግለፅ እንደተሞከረው 1ኛ እና 2ኛ ይግባኝ ባዮች ለግንባሩ ሕገ ወጥ ዓላማ ከግንባሩ አባላት ጋር ለዓላማው ግብ መምታት መተባበራቸውና መርዳታቸው የተረጋገጠባቸው ስለሆነ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጥፋተኞች የተባሉበትን የወ/መ/ሕግ ቁጥር 252(1)(ሀ) በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 113(2) መሠረት በመለወጥ ለዚህ ድርጊታቸው አግባብነት አለው ባልነው የወ/መ/ሕግ ቁጥር 32(1)(ሀ) እና 269 (ሐ) ሥር ጥፋተኞች ናቸው ብለናል።

ይግባኝ ባዮች ጥፋተኞች የተባሉበት የወ/መ/ሕግ ቁጥር 269(ሐ) እንደነገሩ ሁኔታ ከአንድ ወር እስከ 10 /አሥር/ ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እሥራት ያስቀጣል።

እነዚህ ይግባኝ ባዮች ተሳትፎ ያደረጉበት የወንጀል ተግባር ከባድ መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። አድራጎታቸው ሊያስከትል ይችል የነበረው አደጋም በቀላሉ የሚታይ አይሆንም።

ስለቅጣት በወ/መ/ሕግ ቁጥር 86 ላይ የተገለፀውን መሠረት በማድረግ እንዲሁም ቅጣትን አስመልክቶ ከግራ ቀኙ ተከራካሪዎች የተሠጠውን አስተያየት በማገናዘብ ጭምር 1ኛው ይግባኝ ባይ ዶክተር ታዬ ወ/ሰማያትና 2ኛ ይግባኝ ባይ አቶ ገ/ፃድቅ ኃ/ማርያም በዚህ ጉዳይ እስካሁን የታሠሩት እየታሰበላቸው ጥፋተኞች በተባሉበት የወ/መ/ሕግ ቁጥር

32(1)(ሀ) እና 269(ሐ) መሠረት እያንዳንዳቸው በ05 /አምስት/ ዓመት ፅኑ እሥራት እንዲቀጡ ወስነናል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሠጠው ውሣኔ በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 195(2)(ለ)(1) መሠረት በዚህ መልኩ ተሻሽሎ መወሰኑን እንዲያውቀው የውሣኔው ቅጂ ይተላለፍለት፡፡

<u>ት ዕ ዛ ዝ</u>

የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በተሻሻለው ውሣኔ መሠረት እንዲፈፅም ይፃፍለት፡፡

ቁጥር 4780/88 የሆነው የከፍተኛ ፍ/ቤት መዝገብ እና ማስረጃዎቹን የያዘው ጥራዝ ለፍ/ቤቱ ይመለስ፡፡ 3ኛው ይግባኝ ባይ እንዲለቀቅ ይፃፍ፡፡ በትዕዛዝ የመጣው 1ኛው ይግባኝ ባይ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፃፋቸው 2 ደብዳቤዎች ዩኒቨርሲቲው እንዲመለሱለት የጠየቀ በመሆኑና ጉዳዩም ስላለቀ ይመለሱለት፡፡

- የፖሊስ የምርመራ መዝገብም ተመልሶ ይላክ

በዚህ መዝገብ የተሠጠው ውሣኔ ቅጂ በወ/ይ/መ/ቁ. 4396, 4349, 4351 እና 4350 በሆኑት መዝገቦች ላይ ይያያዝ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የዳኞች ፊርማ - ተገኔ ጌታነህ

ሆሣዕና ነጋሽ

አሰግድ ጋሻው

ፌዴራል ጠቅላይ ... ትክክለኛ ግልባጭ ... ቀን 5·9·84